# <u>*በኮለምቦስ ኦሃዮ የአምባገነኑና የዘረኛው ህወሓት ተላላኪዎች የጠሩት ስብሰባ፡ አሳፈሪ በሆነ መልኩ ተገባደደ።*</u>

*ሚያዝያ* 9 *ቀን* 2011 *ዓ/ም አምባገነኑና ዘረኛው ወያኔ አስነዋሪና አሳፋሪ በሆነ መልኩ በኮሎምቦስ ኦሃዮ በሒያት ሪጀንሲ ሆቴል በጠራው ስብሰባ አብዛኛውን ኢትዮጵያዊ ያገለለ፣ ነገር ግን ጥቂት ህሊናቸውን ለጥቅም በሸጡ፣ በአካባቢው ህብረተሰብ በርካሽ ስነምግባራቸው በሚታወቁ፣ ራስ ወዳድ ግለሰቦች፣ የተወሰኑ ሶማሌዎችና የኤርትራ ተቃዋሚ አባላት ነን የሚሉ ሰዎች ብቻ የተገኙበት ውጤታማ ባልሆነ መልኩ ተከናውኗል። የወያኔ ካድሪዎች እቅድ፤ በውጭ ሀገር የሚገኘውን ሕብረተሰብ ለማሳሳት፣ ተቃዋሚ ድርጅቶችንም ለመከፋፈል ቢሆንም፡ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የአማራው፥ የኦሮሞው፥ የደቡብ ብሔረሰቦችና የኦጋዴን፥ ሕብረተሰብ የአገራቸውን ሰንደቃላማ ከፍ አድርገው በማውለብለብ ዘረኛውን፣ አማባገነኑን፣ጉጠኛውን ወያኔና ተላላኪዎቹን <u>**በቃ፥ ገዱ፥ የአክል፥ ባስ---**</u> ወዘተ በሚል መሪ መፈክር ጥላ ስር በመሰባሰብ ሲያወግዙ ውለዋል። እንዲሁም በዘር በጎሳ አከፋፍያቸዋለሁ፤ እንግዲህ ለአንድ መቶ ዓመት ስልጣን ከእኛችን የሚያወጣ አካል አይኖርም፤ በሚል እጉል እምነት ሲኩራራ የነበረው ወያኔ፤ ከመቸውም በተለየ መልኩ ከሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችቦችና አገር ወዳዶች ተገናኝተው ወያኔን ያሳፈሩበትና ለወደፊትም የጠላትን ሴራ በጋራ ለመመከት ቆርጠው እንደተነሱ ቃል የገቡበት መልካም አጋጣሚ ነበር።*

*የዘረኛው ቡድን ቁንጮ የሆነውን የመለሰ ዜናዊን ዓላማ አንግበው ወደ መሰብሰቢያ አዳራሻ ይገቡ የበሩ ቀኑ የጨለመባቸው የወያኔ ካድሬዎችና ጥቂት ሆዳሞች ባጋጠማቸው ከፊተኛ የሕዝብ ተቃውሞ፡ ተደናግጠው በፍርሃት አንገታቸውን አቀርቅረው እየተርበተበቱ ለመኳዝ ተገደዋል። ከሕዝብ ወገን የቆሙት የቁርጥ ቀን ልጆች ግን ግልጽ ዓላማቸውን ለሚመለከታቸው የመንግሰት ባለሰልጣናትና ለአላፊ አግዳሚው ለምን ወያኔን እንደሚቃወሙትና እንደሚያወግዙት የሚገልጹ ጠንካራ መልዕክት ያዘሉ ጹሑፎችን በማሰራጨት ተልዕኳቸውን በአግባቡ ተወጥተዋል። ዝግጅታቸውም ሰምሮ ታይቷል።*

*የተቃውሞ ሰልፍ አስተባባሪዎች በወቅቱ በተገኘው ድል ረክተው ተጨማሪ ውጤቶችን ለማስመዝገብ ይረዳ ዘንድ የዘር፥ የኃይማኖት፥ የቋንቋ እንዲሁም የአመለካከት ልዩነቶች ሳያሳዩ በጋራ ለመታገል አንድ ጊዜያዊ ግብረኃይል አቋቁመዋል። ስለሆነም ከዚህ በታች የተጠቀሱትን የአቋም መግለጫ አውጥተዋል።*

1. *ነፃና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያ ሳይሰፍን ልማት ሰለማይመጣ፣ ወያኔ የ*5 *ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን የሚለው እቅድ የማደናገርያና በስልጣን ለመቆየት የሚጠቀምበት ፕሮፐጋንዳ ስለሆነ አጥበቀን እንቃወመዋለን።*

2. *በኢትዮጵያ ውስጥ በፖለቲካ አመለካከታቸው ለእስር የተዳረጉት በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎች በአስቸኳይ እንዲለቀቁ እንጠይቃለን።*

3. የአምባገነኑና የዘረኛው የወያኔ ሥርዓት ለረጅም ዓመታት በሐገራችን ላይ እየፈፀመ ያለውን እጅግ ዘግናኝ ኢሰብአዊ ድርጌት ለዓለም መንግሥታት፣ ለሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅቶችና ለመላው የዓለም ሕዝብ ለማጋለጥ የሚጠበቅብን ግዴታ በአግባቡ እንወጣለን።

4. የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃና ሚዛናዊ የሆነ የዜና ዘገባና መረጃ ማግኘት የዲሞክራሲ መብቱ ስለሆነ ወያኔ በመገናኛ በዙሃን ማለት በጋዜጦች፥ በሬድዮ፥ በቴሌቪዥን ላይ የሚያደርገውን ሕገ ወጥ ተግባር በአስቸኳይ እንዲያቆም እንጠይቃለን፡ በተለይም ዓለም አቀፍ እውቅና በተሰጣቸው በአሜሪካና በጀርመን ራድዮ ጣቢያዎች ላይ  የሚያደርገውን አፈና አጥብቀን እንቃወማለን፣ ድርጊቱንም እናወግዛለን።

5. በወያኔ አባላትና ደጋፊዎች በተያዙና በሚተዳደሩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ላይ የኢኮኖሚ ማዕቀብ እንዲጣል ያላሰለሰ ጥረት እናደርጋለን። ሌሎችም ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ እናበረታታለን።

6. በለፈው ስርዓት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሲጨፈጭፉ፡ የነበሩ አንዳንድ ወንጀለኞች ዛሬ በህወሓት ጥላ ስር ተከልለው ዳግም ወንጀል ለመፈጸም በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች ለወደፊቱ በሕግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ከወዲሁ መረጃዎችን የማሰባሰብ እንቅስቃሴ  ጀምረናል።

7. የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ሲታግልለት የነበረና አሁንም በየዘርፉ እየታገለለት ያለውን የዲሞክራሲ ጥያቄ ከግቡ እንዲደርስ ሁሉም የተቃዋሚ ድርጅቶች ጥቃቅን ልዩነቶች ላይ ትኩረት ከመስጠት ተቆጥበው፡ በአንድነት በመቆም በዋናው ጠላታቸው በወያኔ ላይ ክንዳቸውን አስተባብረው ጠንክረው እንዲሰሩ እናሳስባለን፡ ለዚህም የሚጠበቅብን ሁለንተናዊ ድጋፋችንን ለመስጠት ቃል እንገባለን።

ኢትዮጵያ በአንድነቷ ለዘላለም ፀንታ ትኑር!

በኮሎምቦስ ኦሃዮ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን።